# አለመቻቻል ወይስ ለጭቆና አለመንበርከስ?

ከመላኩ ይስማው

ሶስት ምሁሮች ከዚህ ቀደም (ጥር 1998) "ያለመቻቻል ፖለቲካ ሰማዕት" በሚል ጽፈው የነበረው ነው ለዚህ ጽሁፍ ያነሳሳኝ። ሰዎቹ ባህሩ ዘውዴ፤ ታደሰ ገሰሰና የራስወርቅ አድማሴ ናቸው። ታደሰና የራስወርቅ መኢሶኖች የነበሩ ሲሆን ዶክተር ባሕሩ ደግሞ ጥቂት ጊዜ የኢሕአፓ አባል የነበር ነው። ዕይታችው ገጥሞ መገኘቱ መቸም ሊያስገርም ይችል ይሆናል።

ሶስቱ ያለመቻቻል ፖለቲካ ሰማዕት የሚሉዋቸው በነጻ እርምጃና በቀይ ሽብር የተገደሉትን ዜጎች ነው። ዋናው መልዕክታቸውም መቻቻል ቢኖር ኖሮ ዕልቂቱ ባልመጣ የሚል ነው። ዶር ባሕሩ ስለ ቀይ ሽብር በእንግሊዝኛ በጻፈው ጽሁፍም ደርግን ሳይሆን ኢሕአፓንና በመለስተኛ ደረጃም መኢሶንን ለደረሰው ዕልቂት ሃላፊ ናቸው ብሎ ሊክስ ሲዳዳውም አንበናል። ያለመቻቻል ጥፋት ነው ባዮች በመሰረቱ ኢሕአፓና መኢሶን ቢቻቻሉ ኖሮ በሚል፣ አያ ደርጉን ዘንጋ፣ ተወት የሚያደርጉ ናቸው። መኢሶኖች ከደርግ ተቻችለው መኖር ይቻላል ብለው ስንቱን ዜጋም ፈጅተውና አስፈጅተው ካበቁ በህዋላ አለመቻሉን ወዳጃቸው ደርግ ደማቸውን አፍሶ ትምህርት እንደሰጣቸው የታየ ሃቅ ነው። መቻቻል ዛሬም ይነሳልና በያኔው ሁኔታ ምን ማለት ነበር? ደርግን ከነግሳንግሱ መቻል--መቀበል። ኢሕአፓና መኢሶን የተለያዩበት ምክንያት ደርግን መደገፍ አለመደገፍ በሚለው ዓቢይ ጉዳይ ላይ ነው። መኢሶን በሂሳዊ ድጋፍ ከደርግ ጋር እንስራ ሲል ኢሕአፓ ደግሞ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይመስረት የሚል አቋም ነበረው። ሁለቱ ተቃራኒ አቋሞች ሊስማሙ ይችሉ የነበሩት አንዱ የሌላውን አቋም ከተቀበለ ብቻ ነበር። መቻቻል ማለት ደርግን መቀበል ማለት ነበር። ሁለቱ ድርጅቶች ቢስማሙም ኖሮ የደርጉን ጸረ ሕዝብነት የሚለውጥ አልነበረም። መሰረታዊ የአቅዋም ልዩነትን በመቻቻል ሽፋን ማስተናገዱ ብልህነት ሳይሆን አድርባይነት ነው። እራስን ለነገ እርድ አመቻችቶ መስጠት። ለዚህም ነው ሰማዕትን ያረመኔው ደርግ ሰለባዎች ማለት ሲገባ ያለመቻቻል ፖለቲካ ሰማዕት ማለቱ ከስህተትም አልፎ ወንጀል የሚሆነው።

ለነጻ እርምጃና ቀይ ሽብሩ ዋና ተጠያቂ የኮሎኔሉ አገዛዝ ነው። ይህን ለመሸፋፈን የመሞከር ጥረት ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው። ሰማዕቱ የቀይ ሽብር ሰለባዎች እንጂ ያለመቻቻል ፖለቲካ ሰለባዎች አይደሉም። ለሕዝባዊ የሥልጣን ባላቤትነት እውን መሆን ጥያቄ አንስተው በሕዝባዊነት ትግል የተሰው ናቸው። ታሪክን በዚህ መልክ ለመሸፋፍን መነሳት አሳፋሪ ነው።

ግፍ ነው ግፍን መርሳት፣
ከገዳይ መዋዛት፣
ከገዳይ መዳራት፣
የሠማዕታት ሥጋ፣ ቦጫጭቆ በመብላት፣
ደም ማወራረጃ አድርጎ መጠጣት።

የምንተነፍሰው ብትን አየር ሁሉ፣
የምንጠጣው ሁሉ፣
ደንጊያ፣ እንሰሳ፣ ተክሉ፣
አፈር ሳር ቅጠሉ፣
የምናየው ሁሉ፣
ሀይቅ፣ ወንዝ፣ ምንጬ፣
ሜዳ፣ ጎራ፣ ድጡ፣
የግፍ አበላዎች፣ ቀርተው እንደወጡ፣
አዕላፍ ነፍሶች ፍትህ፣ ጥሪ እሚያስደምጡ፣
ነው መቃብር ቦታ፣ ዳር እሰከዳር ሰርጡ!

ጪኸት ነው ዝምታ፣
ሣቅም ነው ኡኡታ፣
አዕላፍ ነፍሶች ጥሪ፣ የታሪክ ሥሞታ፣
ገድለን የማንገድላት፣ ሀቅ፣ እውነት! እሪታ!

ያዕላፍ ነፍሶች አካል፣ በላዩ ላይ ፈርሶ፣

በተገነባ አፈር፣ ደም ካጥንት ተላቁጦ፣
እየተራመዱ፣ ሠማዕታት ረግጦ፣
የፍትህ ኤሎሄ፣ ጥሪውን ደፍጥጦ፣
ረምርሞ መሄድ፣ እውነትን ሸምጥጦ፣
‘ርም ነው እርግማን፣ ሠባ ቤት ልጅ መብላት፣
ሥጋውን መቦጨቅ፣ ደሙንም መጠጣት!

በግርፋት ብዛት፣ ታርሶ ተተልትሎ፣
በሙቅ ውሃ፣ ዘይት፣ ኤሌክትሪክ ተቃጥሎ፣
የእግር እጅ ጥፍሩ፣ በግፍ ተነቃቅሎ፣
የወደቀ ወገን፣ መኖሩን አብሎ፣
ግፍ ነው ግፍን መርሣት፣
ታሪክን ከሚገል፣ ከገዳይ መተኛት!

የታሪክ ምፀቱ፣ እያየንም ባናይ፣
ከባሮ፣ ከኦሞ፣ ከአዋሽም፣ ካባይ፣
የሚብልጥ ደም ጎርፏል፣ ጦቢያ ምድር ላይ!

ሥጋ ነው አፈሩ፣ የጭንቅላት ፍራሽ፣
ደም ነው በጠቅላላው፣ የምንጠጣው ፈሳሽ፣
ለሚያነብ ህሊና፣ ታሪክን አስታዋሽ!
ስለሠማዕታቱ ፣ህያው ችሎት ከሳሽ!

ካድማስ አድማስ ድረስ፣ ለሆሣስ ተሰምቶ፣
ጀሮ እሚዠልጠው፣ በዝም አስተጋብቶ፣
ያዕላፍ ሠማዕት ለቅሶ፣
የራሄል ሰቆቃን፣ አሎሄ አሰምቶ፣
ሠሚ ያጣ ጬኸት፣ ለፍትህ ተጣርቶ፣
ለመቅበር መቆፈር፣ ደቦ ተጠራርቶ፣

ግፍ ነው ግፍን መርሳት፣
ከገዳዩ ጋራ፣ ድሪያ በመዳራት፣
ሥጋውን በመብላት፣
ደሙንም መጠጣት!

ጸረ ወያኔ ትግል ሊፋፋም ሲገባም ይህን ርባና ቢስ የመቻቻል ፖለቲካ መስበክ የሕዝብን ትግል ማኮላሸት፣ መጉዳት ነው። የትላንት ታሪክ ላይ በመዋሸት ዛሬም ተመሳሳይ ስህተት ለመድገም መጣር አይጠቅምም። ትላንት የነመኢሶን ከወታደራዊው አገዛዝ መዳራት ሕዝባዊውን ትግሉንም፣ እነሱንም አልጠቀመም። እውነተኛ ሕዝባዊ ጥያቄ ያነሱ ታጋዮችን አብሯቸው ከበላ በሁዋላ እነሱንም በላቸው። ለመሆኑ አሁን ባለው የጸረ-ወያኔ ዘረኛ ትግላችን ከእነልዴቱ ታማኝ አገልጋይነት፣ ከነፕሮፌሰር መስፍን የ"ልጆቻችን ናቸው" ሰበካ፣ ከሌሎቹም የፓርላማ በረት ወንበር አሟቂ ተላላሽ ተ"ቃዋሚ" ተብዬዎች ምን አተረፍን? ትላንትን በተንሸዋረረ መነፀር እያየን ከታሪክ ካልተማርን ዛሬም ተመሳሳይ ስህተት ደጋግሞ መፈፀማችንን አናቆምም። መቻቻል የሚል አጉል ሰበካ ጭቆናን ለመሸከም ደንደሳችሁን አጠንክሩ ከማለት ሌላ ፍች የለውም።